# ሃይማኖትን እና ፖለቲካን የማዳበል ጣጣ!

ቢላል አል-ጀበርቲ 01/06/14

በታሪክ ውስጥ ሰዎች ፈለጉም አልፈለጉም የገሃዱ ዓለም ነባራዊ ሂደት ይፋ ሲያወጣው የሚስተዋል ምስጤራዊ እውነታ ያጋጥማል። ይህን ተጠየቃዊ ይዘት ካለው መሰረተ ሃሳብ የሚመነጭ መከራከሪያ እንዳነሳ ምክንያት የሆነኝ ከጥንታዊቷ ግሪክ ታላላቅ አዕምሮዎች እንደፈለቀ የሚነገርለትን የዘመናዊው ዓለም ፍልስፍና ከማንበብ ያገኘሁት ዕውቀት አይደለም።

ይልቁንስ በዛሬዋ ግብጽ ፖለቲካዊ ሂደት ውስጥ ከሚታየው እጅግ በጣም አስገራሚ ሊባል የሚችል ክስተት በስተጀርባ የሚገኙ አንዳንድ ታሪካዊ እውነታዎች ናቸው። እነሱን መንደርደሪያ አድርጌ ትዝብቴን እንድተነፍስም ገፋፍቶኛል።

መቸስ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ኢትዮጵያን ጭምር ሲፈታተነን የሚስተዋለው የሃይማኖት አክራሪነት ለማንኛውም ሃገር ፖለቲካዊ ችግር አንዳች ጠቃሚ ትምህርት ሊያስተላልፍል አይችልም፡፡ በዚህ መነሻነት የግብፅን ክራሞት ከብዙ በጥቂቱ ለመቃኘት ፈልጌያለሁ።

“የአረቦች ፀደይ” የሚል ስያሜ በተሰጠው የተቃውሞ ንቅናቄ ከመንበረ ስልጣናቸው እንዲወርዱ ከተገደዱት የሰሜን አፍሪካ ሀገራት መሪዎች መካከል አንዱ የሆኑት የቀድሞው የግብፅ ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ በጣህሪር አደባባይ የለውጥ ፈላጊዎች አመፅ ተሸንፈው ወደ ዘብጥያ መውረዳቸው የቅርብ ግዜ ታሪክ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ በግብፅ ፖለቲካ ውስጥ መጣ የተባለው “ስር ነቀል ለውጥ” እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሃገሪቱ እያስተናገደች ያለችው ተጨባጭ እውነታ አራምባና ቆቦ ሆኗል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የበኩሌን አስተያየት ለመግለፅ እችል ዘንድ የጉዳዩን ታሪካዊ ዳራ መመልከት አስፈላጊ ያደረገዋል።

እናም ዛሬ በአፀደ ህይወት የሌሉት የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በግብፅ ፖለቲካ የተስተዋለውን የመንግስት ለውጥ ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ መገንባት ከጀመረችው ታላቁ የህዳሴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ ጋር

አያይዘው እንዲገልፁ በጋዜጠኞች ተጠይቀው ነበር። እርሳቸው የሰጡት ምላሽ አሁን እየሆነ ካለው እውነታ ጋር ሲነፃፀር ሰውየው ምን ያህል አርቆ የመመልከት ብቃት እንደነበራቸው በይበልጥ እንድንገነዘብ የሚያደርግ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በዚህ ዙሪያ ተጨባጭ ምሳሌዎችን እያጣቀስን ለመመልከት እንችል ዘንድም እነሆ ንግግራቸውን (ቃል በቃል ባይሆንም) እጠቅሳለሁ።

*… በመሰረቱ አሁን ግብፅን ጨምሮ በአንዳንድ የሰሜን አፍሪካ አገሮች የተቀሰቀሰውን ተቃውሞና የተቃውሞው ግፊት ያስከተለውን ፖለቲካዊ ክስተት ወይም የመንግስት መቀያየር ሙሉ በሙሉ ያለቀለት ጉዳይ አድርጎ መውሰድ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም።*

*ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት ያልተጠበቀና መነሻውም ሆነ መድረሻው በውል ያልታወቀ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ብዙውን ጊዜ ህዝቡ ሚፈልገውን ስር ነቀል የስርዓት ለውጥ የሚያመጣ ግብ ከመምታት ይልቅ በተቃራኒው አቅጣጫ ተጉዞ ወደባሰ ቀውስ የሚያስገባ አደጋ ላይ ሲጥል የሚታይበት አጋጣሚ ይኖራል።*

*አሁን ግብፅ ውስጥ ያለውን ወቅታዊ የፖለቲካ ትኩሳት ከዚህ አኳያ ስንገመግመው ገና ያልለየላቸውና ያልጠሩ ብዙ ነገሮች አሉ ማለት ይቻላል። ይህ ማለት ደግሞ አዲሱ የዚያች አገር መንግስት ኢትዮጵያን ወይም የአባይን ጉዳይ በተመለከተ ምን ዓይነት ፖሊሲ ይኖረው ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ይጨምራል*

ነበር ያሉት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፤ ከሁለት ዓመት በፊት።

እንግዲህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በግብፅ ፖለቲካ ውስጥ የተስተዋለውን ውጥንቅጡ የወጣ መመሰቃቀልና አሁንም ድረስ የዚያችን ሀገር ዜጎች ደም በማቃባት ላይ ያለውን ችግር ልብ ትሉልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ።

እንደኔ እምነት መለስ ዜናዊ በአፀደ ህይወት ኖረው በመሆን ላይ  ያለውን ሁሉ ለመታዘብ ባይታደሉም፣ በዛሬዋ ግብፅ ፖለቲካ ውስጥ በተግባር ሲገለፅ የምናየውን አስገራሚ ክስተት አቶ መለስ አስቀድመው ተረድተውት እንደነበር ግን ደፍሮ መናገር የሚቻል ይመስለኛል።

በተለይ ደግሞ ሆስኒ ከስልጣን ከተወገዱ በኋላ በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላይ አክራሪነትን በማራመድ የሚታወቀው የሙስሊም ወንድማማቾች ማህበር እንደ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ተቆጥሮ መወዳደሩና ከቶውንም አሸንፎ በትረ ስልጣን እንዲጨብጥ መደረጉ ሲታይ፣ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት የተከሰተው የግብፃውያኑ ለውጥ ፈላጊዎች ንቅናቄ በእርግጥም ብዙ ያላለቀ ጉዳይ እንደነበረበት አምነን እድንቀበል የሚያስገድድ ነው ።

ለምን ቢባል የግብፁ "ሙስሊም ብራዘርስሁድ" የሙስሊም ወንድማማችነት ማሰባሰቢያ ማህበር ማለት ሲሆን ሲሆን፣ ዓለምን በጠቅላላ፣ ያን ማድረግ የሚያዳግት ከሆነ ደግሞ መላውን የአረብ ሀገራትና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ህዝቦች ያሉበትን የምድራችንን ጥግ ሁሉ የሚያጠቃልል አንድ ኢስላማዊ መንግስት የመመስረትን ዓላማ አንግቦ ከነአልቃይዳ በፊት የተቋቋመ የአክራሪነት ጠንሳሽ ቡድን መሆኑ ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ነው።

ታዲያ የአልቃይዳው መስራች ኦሳማ ቢላደንና እርሱን ተክቶ ዓለም አቀፋዊውን የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ በመምራት ላይ የሚገኘው ግብፃዊው አይማን አልዘዋሒሪ እንዲሁም ሌሎች ቱባ ቱባ የሽብር ፈጠራው መረብ አባላት ጭምር አሁን የሆኑትን እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል ተብሎ የሚነገርለት የሙስሊም ወንድማማችነት ማህበር ነው፡፡ ከቱኒዚያ ተጀምሮ ወደ ግብፅ የተዛመተውን "የአረቦች ፀደይ" እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የዚያችን ሀገር ፖለቲካዊ ስልጣን መጨበጥ ሲችል ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሲያልመው የኖረውን በአንድ እስላማዊ ስርወ መንግስት ወይም "ኢስላሚክ ኢምፓየር" ስር የምትተዳደር ዓለም የመፍጠር አጀንዳውን ለማሳካት የሚያስችል እንቅሰቃሴ ሲያደርግ ቢስተዋል ሊያስገርም ይገባልን!?

እንደኔ እምነት፣ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት እንደቀልድ የተቀሰቀሰውን "የአረቦች አብዮት" እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው የግብፅ ሉአላዊ መንግስት ፕሬዚዳንትነትን ስልጣን የጨበጡት ሞሐመድ ሙርሲና ለዚህ ወግ ማዕረግ ያበቃቸው የሙስሊም ወንድማማችነት ፓርቲ፣ ለዘመናት የታገሉለትን "ዓላማ" እውን ለማድረግ የሚያስችላቸውን ወርቃማ ዕድል እንዳገኙ ቆጥረው ጊዜ ሳያጠፉ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ቢጀምሩ የሚጠበቅ እንጂ የሚያስገርም ክስተት አይደለም።

ስለዚህ ሰሞኑን የግብፅ ጦር ሃይል የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ የተሰኘውን የአክራሪዎች ቡድን በሽብርተኝነት እንደፈረጀው ይፋ ማድረጉ ከመዘግየቱ በስተቀር ተገቢነቱ የሚያከራክር ጉዳይ እንደማይሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። እንደ ኢስላሚክ ብራዘርሁድ ዓይነት ሃይማኖታዊ ካባ ያጠለቁ ፖለቲከኞች አንድ ሉዓላዊ ሀገርን የመምራት ስልጣን እንዲይዙ ዕድል የሚሰጣቸውን መሰል ስህተት መፈጸም እንደ ተራ ስህተት ሊቆጠር አይገባም። "በተለይ ደግሞ እንደ አልቃይዳ ዓይነቶቹ ዓለም አቀፋዊ የሽብርተኝነት መረቦች ለእስልምና እምነት ተከታዮች ህዝቦች መብትና ነፃነት የቆሙ

መስለው ከሚያደርጉት ስውር እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ሲታሰብ ሊያስከትል ከሚችለው አደጋ አኳያ ግብፃውያኑ ወታደራዊ መኮንኖች የጉዳዩን አሳሳቢነት በቅጡ መገንዘባቸውና የእርምት እርምጃ ለመወሰድ መቻላቸው የጦር ሃይሉ ታሪካዊ ሃለፊነቱን እንደተወጣ ሊያስቆጥረው ይችላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ዛሬም ድረስ መቋጫ ባልተገኘለት የዕርስ በርስ ደም መፋሰስ ታጅቦ እየቀጠለ ያለው የግብፅ ፖለቲካዊ ቀውስ የፈጠረው ታሪካዊ ስህተት የሚመነጨው፣ ለተከታታይ 18 ቀናት በዘለቀ የጣህሪር አደባባይ ተቃውሞ የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክን መፈናፈኛ አሳጥተው ከመንበረ-ስልጣን እንዲወርዱና ለእስር እንዲዳረጉ ያስገደዷቸው ግብፃውያን ለውጥ ናፋቂዎች ካሳዩት ገደብ የለሽ ስሜታዊነት  ነው።

ከዚያም “የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል” እንዲሉ የሙስሊም ወንድማማቾች አክራሪ ቡድን አባላት እውነተኛ የስርዓት ለውጥ ፍለጋ አደባባይ የወጣውን ግብፃዊ ዜጋ ጭምር እያጋጋሉ ለእነርሱ ድብቅ አጀንዳ መሳካት ተጠቀሙበት፡፡ በዚህ አካሄድ የዚያች ሀገር ቀጣይ ዕጣ - ፈንታ ከዘመነ ሙባረክ የተሻለ እንዲሆን የሚያስችል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ይፈጥራል ተብሎ የታመነበትን አብዮት ለጠባብ ሃይማኖታዊ ጥያቄያቸው ምላሽ በሚሰጥ መልኩ እንዲቃኝ ተንቀሳቀሱ።

እናም በግብፃውያን የፖለቲካ ባህል እንብዛም ያልተለመደ ግብታዊነትን እንዳስተናገደና ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ዓይነት ውጤት እንደነበረው በሚነገርለት ሀገር አቀፋዊ ምርጫ የአክራሪው ሙስሊም ወንድማማች ፓርቲ መሪ የሆኑት ሞሐመድ ሙርሲ እንዳሸነፉ ተረጋገጠና ሰውየው ሙባረክን ተክተው ካይሮ ወደሚገኘው ቤተመንግስት ይገቡ ዘንድ የታሪክ አጋጣሚ ፈቀደላቸው።

እርሳቸው ግን እንኳንስ የመረጣቸው የግብፅ ህዝብ ተስፋ እንዳደረገው ከሆስኒ ሙባረክ የተሻሉ ሀገር መሪ ሆነው ሊገኙና የለውጥ ሒደቱን አጠቃላይ ቅኝት ለአክራሪው የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ድብቅ ዓላማ ማስፈፀሚያነት በሚያመች ሃይማኖታዊ ወርድና ቁመት እየቆራረጡ መቀጠል ላይ ብቻ ተጠምደው መዋል ማደርን የዕለት ተዕለት ተግባር አድርገው እንደተያያዙት ነው የሚወራላቸው።

ይህ ዓይነቱን እጅግ በጣም ሃላፊነት የጎደለው ድርጊት ፈፅሞ ያልወደደላቸው አብዛኛው ግብፃዊ ዜጋም አዲሱ ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ ያቺን ሀገር ለመምራት የሚያስችል

ብቃትም ሆነ የፖለቲካ ስብዕና ሳይኖራቸው ግርግሩን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ብቻ መመረጣቸውን የተረዳውና ሰውየው ሳይውሉ ሳያድሩ ስልጣናቸውን እንዲለቁ መጠየቅ የጀመረው በጥቂት ወራት ውስጥ እንደነበር።

"ሞሐመድ ሙርሲ አክራሪ ሃይማኖተኛ እንጂ የፖለቲካ ሰው አይደለም። ስለዚህ ለሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን ጠባብ አጀንዳ መሳካት ከመጨነቅ አልፎ የግብፅ ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ መደረጉ ስህተት ነውና በአስቸኳይ ስልጣኑን ለመረጠው ህዝብ እንዲያስረክብ እንጠይቃለን…!" ወዘተ የሚሉ መፈክሮችን ይዞ ዳግም ወደ ጣህሪር አደባባይ የሚወጣው ሰልፈኛ ቁጥር ከቀን ወደቀን እየጨመረ ሲሔድ ነው የጦር ሃይሉ በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባትና የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ የተገደደው።

እናም በጀነራል አብዱልፈታህ አልሴሲ የሚመራው የግብፅ ጦር ሃይል ከፍተኛ መኮንኖች ስብሰብ " በመረጣቸው ህዝብ ላይ ጭምር ሲቀልዱበት ሰንብተዋል" የሚል ክስ የቀረበባቸው ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ አንድ አመት ብቻ ከተቀመጡበት መንበረ ስልጣናቸው እንዲወርዱና የተጣለባቸውን ታሪካዊ ሃላፊነት በአግባቡ እንዳይወጡ ያደረጋቸው መሰረታዊ ምክንያት እንዲጣራ መወሰኑን አሳወቀ።

በዚሁ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ከወታደራዊው ክፍልና ከታዋቂ የሀገሪቱ ምሁራን የተውጣጣ አጣሪ ቡድን ተቋቁሞ የሞሐመድ ሙርሲ ጀርባ ሲጠና፣ ሃይማኖታዊ ጉዳይን ከፖለቲካ አጀንዳ ጋር እያጣቀሱ ለመንቀሳቀስና በሽሪአ ሕግ ብቻ የሚተዳደር እስላማዊ መንግስት የሚመሰረትበትን ምቹ ቅድመ ሁኔታ ለመፍጠር ሲሉ መደበኛውን የፕሬዚዳንትነት ተግባራቸውን ዘንግተውት እንደቆዩ ተረጋገጠ።

አጣሪ ኮሚቴው ይህን ፍንጭ ተከትሎ የሰውየውን ጀርባ የማጥናት ጥረቱን በቀጠለ ቁጥር ደግሞ አጅግ አስደንጋጭ የአለማቀፋዊ አሸባሪነትን ምስጢር የያዙ መረጃዎችን አገኙባቸው ከሙርሲ ላይ።

ከመረጃዎቹ መካከልም ሰውየው የግብፅ ፕሬዚዳንት ሆነው በሰሩባቸው ጥቂት ወራት ውስጥ እንኳን የዚያችን ሉአላዊት ሀገር ብሔራዊ ጥቅሞችና እንዲሁም አጠቃላይ ህልውና ለከፋ አደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ወታደራዊ ምስጢሮችን ሳይቀር ለአልቃይዳው ዓለም አቀፍ የሽብርተኝነት መረብ አንቀሳቃሾች አሳልፈው ሲሰጡ መቆየታቸውን የሚያመለክት እንደሚገኝባቸው ተረጋግጧል።

አሁን ያለው የግብፅ ጊዜያዊ መንግስትም ይህን አሳፋሪ ድርጊት ፈፅመዋል ባላቸው መሐመድ ሙርሲና ግብራበሮቻቸው ላይ በሀገር ክህደት ወንጀል  ክስ እንደመሰረተባቸው አስታውቋል፡፡ የክስ ሂደቱ በበቂ ማስረጃና በሰው የምስክርነት ቃል ከተረጋገጠ ደግሞ እስከ የሞት ፍርድ የሚደርስ ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚችል ነው በጉዳዩ ዙሪያ የወጡ ዘገባዎች ያመለከቱት።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ራሳቸው ሞሐመድ ሙርሲ በሊቀመንበርነት ይመሩት እንደነበር የሚነገርለትና “የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ” በመባል የሚታወቀውን የአክራሪ ሃይማኖተኞች ስብስብ ከነ አልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ሲያደርግ በግብፅ የፀጥታ ሃይሎች ስለተደረሰበት በሽብርተኝነት መፈረጁን የዚያች ሀገር ጊዜያዊ መንግስት ባለስልጣናት ከሰሞኑ ይፋ አድርገዋል።

እንግዲህ ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊት ቱኒዚያ ላይ እንደቀልድ ተጀምሮ ከመቅፅበት ወደ ግብፅና ሊቢያ አልፎም እስከ መካከለኛው ምስራቅ ድረስ ተዛመቶ የነበረው “የአረቦች ፀደይ” የተሰኘ ዱብ ዕዳ ከተስተናገደባቸው ሀገራት ታሪካዊ እውነታ ጠቃሚ ትምህርት የመቅሰም ፍላጎት ላለው ቅን አሳቢ ኢትዮጵያዊ፣ ይህ ፅሁፍ በዋነኛነት ካተኮረበት የግብፅ ፖለቲካ ወቅታዊ ገፅታ ብቻ ብዙ ቁም ነገር መጨበጥ እንደሚቻል ይሰማኛል።

በተለይ ደግሞ እዚህ እኛ አገር ውስጥም ሃይማኖታዊ ጉዳይን ተተግነው የፖለቲካ አጀንዳቸውን የማሳካት ፍላጎት የሚያሳዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሁን አሁን ሲያደርጉ ለሚስተዋለው ያልተገባ አዝማሚያ የግብፁ ሰሞነኛ ክስተት ጥሩ መልዕክት ሊያስተላልፍ የሚችልና የአደጋውን ተጨባጭነት በማመላከት ረገድም ቀላል ግምት የማይሰጠው ይመስለኛል። በተረፈ ግን መልካሙ ነገር ሁሉ አይለየን!